# የክርስቶስ ሰውነት ራእይና፥የመጨረሻው ዘመን አገልግሎቶች

(The Vision of the Body of Christ, and the End Time Ministries)
By *Tommy HIcks*

በቶሚ ሀይክስ

(*"ድውያንን ለመፈወስ" ከሚለው መጽሐፍ፥ገጽ 8-16፥በ ሲ. እና ኤፍ. ሀንተር*)
*(from "To Heal the Sick", pg 8-16, by C. & F. Hunter)*

መልእክቱ ጁላይ 25፥ ከጠዋቱ 2:30 በዊኒፔግ፥ ካናዳ ይጀምራል። **እግዚአብሔር** የሰጠኝ ህልምና መገለጥ ሲመጣልኝ እንቅልፍ የሚባል አልተኛሁም። ህልሙ ሦስት ጊዜ መጣ፥በትክክል ተብራርቶ፥(እ.ኤ.አ) ጁላይ 25፥ 1961 ዓ.ም ጠዋት ላይ። በራዕዩ በጣም ተነቃቅቼና ተነሳስቼ ነበር፥ በ**ክርስቶስ** አካል ላይና በመጨረሻው ዘመን አገልግሎት ላይ ያለኝን አመለካከት ሙሉ በሙሉ ነው የለወጠው።

**የኢየሱስ ክርስቶስ** ቤተክርስቲያን ከተሰጣት ሁሉ የሚበልጠው ወደ ፊት ያለው ነው። ወንዶችና ሴቶችን **እግዚአብሔር** በዚህ በመጨረሻው ዘመን ለሕዝቡ ለመስጠት እየሞከረ ያለውን ነገር እንዲያውቁትና እንዲረዱት ለመርዳት መሞከር በጣም ከባድ ነው።

ከብዙ ሳምንታት በፊት በአፍሪካ ናይሮቢ ውስጥ ሰባኪ ከሆነ አንድ የሀገራችን ልጅ ደብዳቤ ደረሰኝ። ይህ ሰውና ባለቤቱ ወደ ታንጋኒካ በመሄድ ላይ ነበሩ። ማንበብም ሆነ መጻፍ አይችሉም፥ ነገር ግን ከሁለት ዓመታት በላይ ስንረዳቸው ነበር። ወደ ታንጋኒካ ድንበር እንደገቡ፥ አንስተኛ ወደ ሆነች መንደር ደረሱ። መንደሪቱን ከመታው ወረርሽኝ የተነሳ ሰው ሁሉ ከመንደሯ ለቆ እየወጣ ነበር። እያለቀሰ ከነበረ ከአንድ የከተማዋ ተወላጅ ጋር ተገናኙ፥እናም ምን ችግር እንደተከሰተ ጠየቃቸው።

በድንገት ስለሞቱት እናት አባታቸው ነገሩት፥ እናም ከሞቱ ሦስት ቀን ሞልቷቸው ነበር። ለቀው መውጣት ነበረባቸው። ወደ ውስጥ ለመግባት ፈርተው ነበር፤ በጎጆዋ ውስጥ ትተዋቸው ነበር። ተመለሰና የት እንደሆኑ ጠየቃቸው። ወደ ጎጆው ጠቆሙትና አብረውት እንዲሄዱ ጠየቃቸው፥ነገር ግን እምቢ አሉ። ለመሄድ ፈርተው ነበር።

የሀገሬው ተወላጅና ሚስቱ አንድ ወንድና አንድ ሴት ሞተው ወደሚገኙበት ወደዚህች አነስተኛ ጎጆ ሄዱና ወደ ውስጥ ገቡ። በቀላሉ እጁን በ**ጌታ በኢየሱስ ክረስቶስ ስም** ዘረጋ፥ የሰውዬውንና የሴትየዋን ስም ጠራና፥ "በ**ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም** ሕይወት ወደ ሰውነታችሁ እንዲመጣ አዝዛለሁ" አለ። ወዲያውም እነዚህ ከአሕዛብ ወገን የሆኑ **ኢየሱስ ክርስቶስን** አንደ **አዳኛቸው** የማያውቁ ሰዎች ቀና ብለው ተቀመጡና ወዲያውም **እግዚአብሔርን** ማወደስ ጀመሩ። የ**እግዚአብሔር** ኃይልና መንፈስ በእነዚህ ሰዎች ላይ መጣ።

ለእኛ እንግዳና ግርምት ሊመስለን ይችላል፥ነገር ግን ያ የዚህ የመጨረሻው ዘመን አገልግሎት መጀመሪያ ነው። **እግዚአብሔር** ሥራ ፈቶችን፥ ማንም የሆኑትን፥ ተሰሚነት የሌላቸውን፥ ከግምት የማይገቡትን ሊወስድ ነው። እያንዳንዱን ወንድና ሴት ሊወስድና ይህን የ**እግዚብሔርን መንፈስ** በኃይል መፍሰስ ሊሰጣቸው ነው። በሐዋርያት መጽሐፍ ይህን እናነባለን "በመጨረሻዎቹ ቀናት" **እግዚአብሔር** ሲናገር "በሥጋ ሁሉ ላይ **መንፈሴን** አፈስሳለሁ።" **እግዚአብሔር** "በሥጋ ሁሉ ላይ **መንፈሴን** አፈስሳለሁ" ያለውን ምን ማለት እንደሆነ አስተውለነው እንደሆነ አላውቅም። እኔ ሙሉ በሙሉ አውቄዋለሁ ወይም ተረድቼዋለሁ ብዬ አላስብም፥

እናም ከዚያ ከትንቢተ ኢዩኤል ላይ አነበብሁ፤ "ኢዩ.2:23፤ *እናንተ የጽዮን ልጆች፥ አምላካችሁ እግዚአብሔር የፊተኛውን ዝናብ በጽድቅ ሰጥቶአችኋልና፥ እንደ ቀድሞውም የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ አዝንቦላችኋልና በእርሱ ደስ ይበላችሁ፥ ለእርሱም እልል በሉ።*" ዝናቡ ብቻ አይደለም የሚሆነው፥ የፊተኛው ዝናብና የኋለኛው ዝናብ፥ ነገር ግን **እርሱ** በዚህ ዘመን የ**እግዚአብሔር**ን ኃይል እጥፍ አድርጎ ለሕዝቡ ሊሰጥ ነው!

ከተኛሁ በኋላ ራእዩ ወደ እኔ ሲመጣ፥ በድንገት ራሴን ከፍ ባለ ርቀት ላይ አገኘሁት። የት ነበርሁ፥ አላውቀውም። ነገር ግን ወደ ምድር ቁልቁል እየተመለከትሁ ነበር። በድንገት መላው ምድር ወደ እይታዬ መጣ። ሀገራት ሁሉ፥ ነገድ ሁሉ፥ ልሳን ሁሉ፥ ከምስራቅ፥ ከምእራብ፥ ከሰሜንና ከደበቡ ወደ እይታዬ መጡ። ከዚህ በፊት የነበርኩባቸውን ብዙ ሀገራትና ከተማዎች አወቅኋቸው፥ እናም ይህን ታላቁን እይታ ከፊቴ እያየሁ በፍርሀትና በመንቀጥቀጥ ነበርሁ፤ እናም ዓለም ወደ እይታ በመጣችበት ቅጽበት፥ መብረቅና ነጎድጓድ ጀመረ።

መብረቁ በምድር ገጽ ላይ ሲያንጸባርቅ፥ ዓይኔ ቁልቁል ተወረወረና በሰሜኑ ፊትለፊት ሆንሁ። በድንገት እነሆ ታላቅ ግዙፍ (jiant) ተመለከትሁ፥ እናም ትኩር ብዬ ስመለከተው፥ በእይታው ግራ ተጋብቼ ነበር። እጅግ ግዙፍና ታላቅ ነበር። እግሩ የሰሜን ዋልታ ራሱም የደቡብ ዋልታ የሚደርስ ይመስላል። እጆቹም ከባሕር እስከ ባሕር ድረስ ተዘርግተዋል። ይህ ተራራ ይሁን ወይም ግዙፍ (jiant) ይሁን እንኳን ለመረዳት ገና አልጀመርሁም ነበር፥ ነገር ግን ስመለከት ሳለ፥ እነሆ ታላቅ ግዙፍን (jiant) በምድር ላይ ተመለከትሁ። ራሱ (ጭንቅላቱ) ለህይወት ሲታገል ማየት ቻልሁ። ለመኖር ይፈልጋል፥ ነገር ግን ሰውነቱ ከራሱ እስከ እግሩ ድረስ በፍርክስካሾች ተሸፍኗል፥ አንዳንድ ጊዜ ይህ ግዙፍ (jiant) ሰውነቱን ያንቀሳቅስና እንደ መነሳት ይላል። ይህንንም ሲያደርግ፥ በሺህዎች የሚቆጠሩ ትናንሽ ፍጥረታት በሽሽት መሮጥ ይጀምራሉ። አስቀያሚ ፍጥረታት ከግዙፉ (jiant) ሸሽተው ይሮጣሉ፥ እናም ሲረጋጋ ተመልሰው ይመጣሉ።

በድንገት ይህ ታላቅ ግዙፍ (jiant) እጁን ወደ ሰማይ አነሣ፥ ቀጥሎም ሌላኛውን እጁን አነሣ፥ እንዲህ ሲያደርግ እነዚህ ፍጥረታት በሺሆች ሆነው ከዚህ ግዙፍ (jiant) ሸሽተው ከብርሃኑ ወደ ጨለማው የሚገቡ ይመስላሉ።

ቀስ በቀስ ይህ ግዙፍ (jiant) መነሣት ጀመረ፥ ሲጀምርም ራሱና እጆቹ ወደ ደመናው ውስጥ ገቡ። ተነሥቶ በእግሮቹ ሲቆም በላዩ ከነበሩት ከፍርስራሾቹና ከእድፉ ራሱን ያጸዳ ይመስላል፥ **ጌታ**ን እንደሚያመሰግን እጆቹን ወደ ሰማይ ማንሳት ጀመረ፥ እናም እጆቹን ባነሣ ጊዜ የበለጠ ወደ ደመናው ገቡ።

ድንገት፥ ደመናው ሁሉ ብር ሆነ፥ አይቼው የማላውቀው እጅግ የተዋበ ብር። ይህን ክንውን ስመለከት በጣም ታላቅ ነበረና ምን ማለት እንደሆነ መረዳት እንኳን አልጀመርሁም ነበር። እያየሁት በጣም ተነቃቅቼ ነበር፥ እናም ወደ **ጌታ** እንዲህ ብዬ ጮኽኩ፡ "ኦ **ጌታ** ሆይ፥ የዚህ ትርጉም ምንድ ነው?" እናም የእውነት በ**መንፈስ** እንደሆንሁ ተሰማኝ ተኝቼም እንኳን የ**ጌታ** ህልውና ይሰማኝ ነበር።

እናም በድንገት ከዚያ ደመና ታላቅ ፈሳሽ የብርሃን ጠብታ በዚህ ኃያል ግዙፍ (jiant) ላይ መዝነብ ጀመረ፥ እናም ቀስ እያለ፥ ቀስ እያለ፥ ይህ ግዙፍ (jiant) መቅለጥ ጀመረ፥ ራሱንም በምድር ውስጥ ማስጠም ጀመረ፥ እናም ሲቀልጥ፥ ገጽታው ሁሉ በምድር ገጽ ላይ የቀለጠ መሰለ፥ እናም ይህ ታላቅ ግዙፍ (jiant) ዝቅ እያለ መምጣት ጀመረ። የብርሃን ፈሳሽ የምድርን ገጽ ሁሉ ማጥለቅለቅ ጀመረ እናም ስመለከት ይህ ይቀልጥ የመሰለው ግዙፍ (jiant)፥ በድንገት በምድር ገጽ ላይ ሚሊየኖች ሰዎች ሆነ። በፊቴ ያለውን እይታ ስመለከት፥ ሰዎች ከመላው ዓለም ተነስተው ቆሙ! እጆቻቸውን እያነሱ **ጌታ**ን እያወደሱ ነበር።

በዚያው ቅጽበት ታላቅ ነጎድጓድ መጣ ከገነትም የሚያስተጋባ ይመስል ነበር። ዓይኖቼንም ወደ ሰማያት አዞርሁና በድንገት ነጭ የሆነን አካል አየሁ፥ በሚያንጸባርቅ ነጭ - በህይወቴ ሙሉ ካየሁት ነገር እጅግ

የከበረ። ፊቱን አላየሁትም፥ ነገር ግን **ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ** እንደሆነ አወቅሁ፥ እጁንም ወደ ፊት ዘረጋ፥ እንዲህም ሲያደርግ ለአንዱ፥ እናም ሌላው፥ እናም ለሌላው ይዘረጋው ነበር። እናም እጁን በሀገራትና በዓለም ሕዝብ ላይ ሲዘረጋ - ወንዶችና ሴቶች - ወደ እነርሱ ሲጠቁም፥ ፈሳሹ ብርሃን ከእጁ ወደ እነርሱ የሚፈስ ይመስላል፥ እናም ኃያል **የእግዚአብሔር** ቅባት በእነርሱ ላይ መጣ፥ እነዚህም ሰዎች በ**ጌታ** ስም ወደ ፊት መሄድ ጀመሩ።

ለምን ያህል ርዝማኔ እንደተመለከትሁት አላውቅም። ቀናትን ሳምንታትን ወራትን አልፎ የሄደ ይመስል ነበር። እናም እነሆ ይህ **ክርስቶስ** እጆቹን ወደ ፊት መዘርጋቱን ሲቀጥል ተመለከትሁ፤ ነገር ግን በዚያ አሳዛኝ ክስተት ነበር። እጆቹን ሲዘረጋ **የእግዚአብሔርን** ቅባትና **የእግዚአብሔርን** ጥሪ እምቢ ያሉ ብዙ ሰዎች ነበሩ። የማውቃቸው ወንዶችንም ሴቶችንም አየሁ። በእርግጠኝነት **የእግዚአብሔርን** ጥሪ ይቀበላሉ የሚል ስሜት ነበረኝ። ነገር ግን እጁን ለዚህኛው ለዚያኛውም ሲዘረጋ፥ እንዲሁ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ትተው ይሄዳሉ፥ ወደ ጨለማ የሚሄዱ ይመስላል። ጨለማ በሁሉም ቦታ የዋጣቸው ይመስላል።

ይህን ሳይ በጣም ግራ ተጋብቼ ነበር፥ ነገር ግን የቀባቸው እነዚህ ሰዎች፥ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ መቶዎችና ሺሆች ሰዎች፥ በአፍሪካ፣ በእንግሊዝ፣ በራሺያ፣ ቻይና፣ አሜሪካ፥ በዓለም ዙሪያ ሁሉ፥ በ**ጌታ** ስም ወደ ፊት ሲሄዱ **የእግዚአብሔር** ቅባት በላያቸው ነበር። እነዚህ ወንዶችና ሴቶች ወደ ፊት ሲሄዱ አየሁ። ቦይ ቆፋሪዎች፥ አጣቢ ሴቶች፥ ሀብታም ሰዎች፥ ድሀ ሰዎች ነበሩ። በሽባነት፥ በበሽታ፥ በዓይነስውርነትና ደንቆሮነት የተጠቁ ሰዎች አየሁ። **ጌታ** ይህን ቅባት ሊሰጣቸው ሲዘረጋ፥ ጤነኛ ሆኑ፥ የተፈወሱ ሆኑ፥ እናም ወደ ፊት ሄዱ!

ተአምሩ ይህ ነው፥ የከበረው ተአምር ይህ ነው፥ እነዚህ ሰዎች ልክ **ጌታ** እንዳደረገው እጆቻቸውን ይዘረጋሉ፥ እናም በእነርሱም እጅ ውስጥ ያለው ያው (በ**ጌታ** እጅ ውስጥ ያለው) ፈሳሽ እሳት ይመስላል። እጆቻቸውን ሲዘረጉ *"እንደ ቃሌ፥ ሙሉ ሁን (ሁኚ)"* ይሉ ነበር።

እነዚህ ሰዎች በዚህ ታላቅ የመጨረሻው ዘመን አገልግሎት ሲቀጥሉ፥ ምን እንደነበረ ሙሉ በሙሉ አልተረዳሁትም፥ ወደ **ጌታ** ተመለከትሁና እንዲህ አልሁት፥ *"የዚህ ትርጉም ምንድ ነው?"* ከዚያም **እርሱ** "***ይህ በመጨረሻው ዘመን የማደርገው ነው። የደነበያውን (cankerworm)፥ የተምቹን (palmerworm)፥ የኩብኩባውን (caterpillar) እመልሳለሁ - እነርሱ ያጠፉትን ሁሉ እመልሳለሁ። እነዚህ ሕዝቤ ናቸው፥ በመጨረሻው ዘመን ወደ ፊት ይሄዳሉ። እንደ ኃያል ሠራዊት የምድርን ገጽታ ይጠርጋሉ።***"

በዚህ ታላቅ ከፍታ ላይ እንዳለሁ፥ መላውን ዓለም ማየት እችል ነበር። እነዚህ ሰዎች በምድር ገጽ ላይ ወደዚህና ወደዚያ ሲመላለሱ አየሁ። በድንገት አንድ ሰው በአፍሪካ ውስጥ ነበር እናም በ**እግዚአብሔር መንፈስ** እየተወሰደ ነበር፥ ምናልባትም በራሺያ፥ ወይም በቻይና፥ ወይም በአሜሪካ አልያም ደግሞ የሆነ ሌላ ቦታ፥ ሊገለባበጥም/የተገላቢጦሽም-ሊሆን (vice versa) ይችላል። እነዚህ ሰዎች በመላው ዓለም ሄዱ፥ እናም በእሳት ውስጥ መጡ፥ በቸነፈሮችም፥ በርሀብም። እሳትም ሆነ ስደት፥ ምንም ነገር የሚያቆማቸው አይመስልም።

የተቆጡ ሰልፈኞች በሰይፍና በሽጉጥ መጡባቸው። እናም ልክ እንደ **ኢየሱስ**፥ በብዙዎች መሀከል አለፉ ሊያገኙአቸውም አልቻሉም፥ ነገር ግን በ**ጌታ** ስም ወደ ፊት ሄዱ፥ እናም በሁሉም ቦታ እጆቻቸውን ዘረጉ፥ በሽተኞች ይፈወሱ ነበር፥ እውራን ዓይኖችም ይበሩ ነበር። ረዥም ጸሎት አልነበረም፥ እናም ራእዩን ደጋግሜ በአእምሮዬ ውስጥ ካመላለስሁት በኋላ፥ እንዲሁም ብዙ ጊዜ ካሰብሁት በኋላ፥ ምንም ቤተክርስቲያን እንዳልተመለከትሁ አስተዋልሁ፥ ምንም ዓይነት የምእመናን ህብረትም አላየሁም፥ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች በሠራዊት **ጌታ** ስም ይሄዱ ነበር። ሃሌሉያ!

በመጨረሻው ዘመን የ**ክርስቶስ** አገልግሎት በሚሠሩት ሥራ ሁሉ ወደ ፊት ሲሄዱ፥ በምድር ገጽ ለሚገኙት ለብዙሀን ያገለግሉ ነበር። አስርሺሆች፥ ሚሊየኖችም ሳይቀሩ ሰዎቹ ቆመው የመንግሥቱን መልዕክት፥

*የሚመጣውን መንግሥት፥ የመጨረሻይቱን ሰዓት ሲገልጡ ወደ **ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ** ይመጡ ነበር። እጅግ የከበረ ነበር፥ ነገር ግን ያመጹም ደግሞ ያለ ይመስላል፥ እናም ይቆጡና መልእክቱን የሚሰጡትን እነዚያን መልእክት የሚሰጡትን ሰዎች ሊያጠቋቸው ይሞክሩ ነበር።*

***እግዚአብሔር** ለዓለሙ ሁሉ በዚህ መጨረሻው ሰዓት ዓለም ፈጽሞ የማያውቀውን ነገር ሊያሳይ ነው። እነዚህ ወንዶችና ሴቶች ከሁሉም የህይወት ጉዞዎች ናቸው፥ ዲግሪዎች ምንም ማለት ይሆናሉ። እነዚህ ሠራተኞች በምድር ገጽ ላይ ሲሄዱ አየሁ። አንዱ ሲሰናከልና ሲወድቅ፥ ሌላው መጥቶ ያነሳዋል። "ትልቅ እኔ" ወይም "ትንሽ አንተ" የሚባል የለም፥ ነገር ግን ሁሉም ተራራ ዝቅ ብሏል እንዲሁም ሸለቆውም ሁሉ ከፍ ብሏል፥ እናም አንድ ነገር በጋራ ያላቸው ይመስላል - መለኮታዊ ፍቅር ነበረ፥ እነዚህ ሰዎች በጋራ ሲሠሩ፥ አብረውም ሲኖሩ ከእነርሱ የሚፈስ መለኮታዊ ፍቅር። ከማውቃቸው ሁሉ በጣም የከበረ እይታ ነበር። የሕይወታቸውም ዓላማ **ኢየሱስ ክርስቶስ** ነበረ። እነርሱም ቀጠሉ እናም ይህን እይታ እያየሁ ቀናት ያለፉ ይመስል ነበር። ማልቀስ ብቻ ነበር የቻልኩት፥ አንዳንድ ጊዜም እስቅ ነበር። እነዚህ ሰዎች በምድር ገጽ ላይ ሲሄዱ በጣም የሚያስገርም ነበር፥ በመጨረሻው ዘመን (መልዕክቱን) ወደ ፊት (ወደ ግልጽ) እያመጡ።*

*ከራሱ ከሰማይ ላይ ሆኜ ስመለከት፥ የዚህ ታላቅ ፈሳሽ ብርሃን ዶፍ ዝናብ በታላላቅ ጉባኤዎች ላይ ሲወርድ የነበረባቸው ጊዜያት ነበሩ፥ እናም እነዚህ ሰዎች የ**እግዚአብሔር መንፈስ** በእነርሱ ላይ ሲመጣ እጆቻቸውን ያነሱና ለሰዓታት አንዳንዴም ለቀናት **እግዚአብሔርን** ያመሰግኑ ነበር። **እግዚአሔርም** አለ፥ "**መንፈሴን በሥጋ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤**" እናም እየሆነ ያለው በትክክል ይህ ነው። እናም ይህን ኃይልና የ**እግዚአብሔርን** ኃይል ለሚቀበል እያንዳንዱ ወንድና ሴት፥ የ**እግዚአብሔር** ተዓምራት ማለቂያ አልነበራቸውም።*

*ስለተዓምራት አውርተናል። ስለምልክቶችና ድንቆች አውርተናል፥ ነገር ግን በዚህ ማለዳ፥ ጠዋት 4 ሰዓት ላይ፥ ከሀገራችን ተወላጅ የሆነውን ደብዳቤ ደግሜ ሳነብብ ልቅሶዬን ማቆም አልቻልሁም። ይህ የመጀመሪያው የአንድ ሰው ማስረጃ ነው፥ "ምንም አታድርጉ፥ ያልተሰማ ነገር፥" ማነው ሄዶ እጁን ዘርግቶ፥ "በ**ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ** ስም፥ ሕይወት በሰውነታችሁ ውስጥ እንዲፈስስ አዝዛለሁ" የሚለው። በጉልበቶቼ ወድቄ በድጋሚ መጸለይ ጀመርሁ፥ እንዲህም አልሁኝ፥ "**ጌታ** ሆይ፥ ይህ ሰዓት በቶሎ እንደሚመጣ አውቃለሁ!"*

*እናም በድጋሚ፥ እነዚህ ሰዎች በምድር ገጽታ ላይ ሲዘዋወሩ፥ ታላቅ ስደት ከሁሉም ማእዘን የመጣ ይመስላል።*

*በድንገት ሌላ ታላቅ የነጎድጓድ ጭብጨባ ነበር፥ ይህ በምድር ዙሪያ ሁሉ ደግሞ ያስተጋባ ይመስላል፥ እናም ድምጹን በድጋሚ ሰማሁ፥ "**እነዚህ ሕዝቤ ናቸው። የተወደዱት ሙሽራዎቼ ናቸው፤**" ብሎ የሚናገር የሚመስል ድምጽ። እናም ድምጹ ሲናገር፥ ሐይቆችና ተራራዎች ይታዩኝ ነበር። መቃብሮች ከመላው ዓለም ይከፈቱ ነበር፥ የሁሉም ዘመን ቅዱሳን እየተነሱ ይመስላል። እናም ከመቃብራቸው ሲነሱ፥ በድንገት ሁሉም ሰዎች ከየአቅጣጫው መጡ። ከምስራቅና ከምእራብ፥ ከሰሜንና ከደቡብ፥ መጥተውም በድጋሚ ታላቁን ግዙፍ* (giant) *ሰውነት የሚሠሩ ይመስላል። በ**ክርስቶስ** የሞቱት ቀድመው ሲነሱ፥ ልቀበለው ከብዶኛል። እጅግ አስደናቂ ነበር። ፈጽሞ ላልመውና ላስበው ከምችለው ነገር እጅግ የራቀ ነው።*

*ነገር ግን ይህ ሰውነት መገንባት ሲጀመርና፥ በድጋሚ ቅርጽ ሲይዝ፥ የዚህን ኃያል ግዙፍ* (giant) *ቅርጽ መያዝ ጀመረ፥ በዚህ ሰዓት ግን የተለየ ነበር። እጅግ በጣም በተዋበ ነጭ ልብስ ተሸልሞ። ሰውነቱ መገንባት ሲጀምር ልብሶቹ ያለነውርና ያለነቀፋ ነበረ፥ የምድር ሰዎች ከሁሉም ዘመናት ሁሉ በዚህ ሰውነት ውስጥ ያሉ ይመስላል፥ እናም ቀስ እያለ፥ ቀስ እያለ፥ ወደ ሰማይ ከፍ ማለት ሲጀምር፥ "**አሁን ቁጣዬ በምድር ላይ እየፈሰሰ ነው።**" የሚል ሌላ የነጎድጓድ ድምጽ ሲያስተጋባ ሰማሁ። ከምድር ዳርቻዎች ሁሉ የ**እግዚአብሔር** ቁጣ ሊፈስ የጀመረ ይመስላል እናም በ**እግዚአብሔር** ቁጣ የተሞሉ ታላላቅ ጽዋዎች በምድር ገጽ ላይ መፍሰስ የጀመሩ ይመስላል። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የተከሰተ ያህል ነው የማስታውሰው። ከተማዎችና መላ ሀገራት በጥፋት ሲወድቁ ሳይ በፍርሀት ተንቀጠቀጥሁ።*

ልቅሶውና ሀዘኑ ይሰማኝ ነበር። ሰዎች ሲያለቅሱ ይሰማኝ ነበር። ወደ ዋሻዎች ውስጥ ሲገቡም የሚያለቅሱ ይመስላል፥ነገር ግን በተራራዎች ያሉት ዋሻዎችም ተከፈቱ።

ወደ ውኃዎች ውስጥ ይዘላሉ፥ ውኃው ግን አያሰጥማቸውም። ሊያጠፋቸው (ሊገድላቸው) የሚችል ምንም አልነበረም። ህይወታቸውን ለማጥፋት እየፈለጉ ነበር፥ ነገር ግን አልቻሉም። ከዚያም ዓይኔን ወደ ከበረው እይታ አዞርሁ፥በሚያምር ነጭ፥አንጸባራቂ ልብስ፥ወደ ተሸለመው ሰውነት። ቀስ እያለ፥ቀስ እያለ፥ከምድር ከፍ ማለት ጀመረ፥ እንደዚያም ሲሆን፥ ነቃሁ። ምን ዓይነት እይታ ነው ያየሁት! የመጨረሻውን ዘመን አገልግሎት፥ የመጨረሻይቱን ሰዓት አይቻለሁ። እንደገና በጁላይ 27፥ ጠዋት 2:30፥ ያው መገለጥ፥ ያው ራእይ እንደ መጀመሪያው ተመልሶ መጣ።

በመጨረሻው ዘመን እየኖርን እንደሆንን ሳስተውል ህይወቴ ተቀየረ፥ በዓለም ዙሪያ ሁሉ **እግዚአብሔር** ወንዶችና ሴቶችን በዚህ አገልግሎት እየቀባ ነው። ዶግማ አይሆንም። ቤተክርስቲያናዊነት አይሆንም። **ኢየሱስ ክርስቶስ** ብቻ ነው የሚሆነው። **የጌታን ቃል** ወደ ግልጽ ያመጣሉ፥ እናም "*በራእዬ ውስጥ ብዙ ጊዜ ሰምቼዋለሁ እናም እንደ ቃሌ እንደዛው ይሆናል*" ይላሉ።

ኢዩኤል.2:25፤ *የሰደደሁባችሁ ታላቁ ሠራዊቴ አንበጣና ደጎብያ ኩብኩባና ተምች የበላቸውን ዓመታት እመልስላችኋለሁ።*

ሮሜ.8:35 *ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ወይስ ጭንቀት፥ወይስ ስደት፥ወይስ ራብ፥ወይስ ራቁትነት፥ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን? ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን፥እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን :ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው። በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።*

ዮሐ.16:1-3 *እንዳትሰናከሉ ይህን ተናግሬአችኋለሁ። ከምኵራባቸው ያወጡአችኋል፤ ከዚህ በላይ ደግሞ የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል። ይህንም የሚያደርጉባችሁ አብንና እኔን ስላላወቁ ነው።*

1ተሰ.4:16-17 *ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።*

ኢሳ.2:11፤ *ከፍ ያለችውም የሰው ዓይን ትዋረዳለች፥ የሰዎችም ኵራት ትወድቃለች፥ በዚያም ቀን እግዚአብሔር ብቻውን ከፍ ከፍ ይላል።*

2ቆሮ.9:12 *የዚህ ረድኤት አገልግሎት ለቅዱሳን የሚጎድላቸውን በሙሉ የሚሰጥ ብቻ አይደለምና፥ነገር ግን ደግሞ በብዙ ምስጋና ለእግዚአብሔር ይበዛል፤*

በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥አሜን።
ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu, shalommuluneh@gmail.com